# የአማራ ክልል የህዝብ ቆጠራ ውጤትን በፓርላማ የብአዴን/ኢህአዴግ አባላት ጭምር ተቃወሙት

በ1999 ዓ.ም በሀገሪቱ በተካሄደው 3ኛው አገር አቀፍ የሕዝብና የቤት ቆጠራ የአማራ ክልል ውጤት ከቅድመ ትንበያው ጋር በ2.4 ሚሊዮን ያህል ልዩነት በመታየቱ ጉዳዩ እንዲጣራና አስፈላጊነቱ ተረጋግጦ ድጋሚ ቆጠራ እንዲደረግ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ውሳኔ አሳልፎ ነበር።

በዚሁ መሰረት የሕዝብና የቤት ቆጠራ ኮሚሽን በሰጠው አመራር የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር አማካሪዎችን ቀጥሮ ማጣራት ሲያደርግ ቆይቶ ውጤቱን ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቧል። በተደረገው ማጣራት፣ የአማራ ክልል የሕዝብ ቆጠራ ውጤት ከቅድመ ትንበያው ጋር በ2.4 ሚሊዮን ህዝብ ሊቀንስ የቻለው "በክልሉ የሞትና የውልደት ምጣኔ ከፍ ተደርጎ በመታሰቡ እና በህዝቡ ፍልሰት" ምክንያት እንደሆነ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ገልፆ፣ በክልሉ የሞት ቁጥሩ ከፍ ሊል የቻለው ደግሞ "በHIV/AIDS" ምክንያት እነደሆነና የክልሉ ህዝብ ፍልሰት ሊታወቅ ያልቻለው ደግሞ "ህዝቡ ያልተማረ በመሆኑ ከየት መጣህ ሲሉት የመጣበትን ዞን ለመግለጽ ባለመቻሉ ነው" የሚል ማብራሪያ ሰጥቷል።

ይህንን የኤጀንሲውን ትንታኔና አስተያየት የሰሙ የብአዴን/ኢህአዴግ አባላት ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ምክር ቤቱን በጫጫታና "ስነ-ስርዓት" በሚሉ አስተያየቶች ሲያስጨንቁ እንደነበር ከስፍራው የደረሰን መረጃ አመልክቷል። "የአማራ ክልል ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ 'በHIV/AIDS' ይሞታል፣ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ይፈልሳል፣ ከየት መጣህ ሲባል የመጣበትን ዞን አያውቅም" የሚሉት አገላለፆች ብዙዎችን የብአዴን/ኢህአዴግ የፓርላማ አባላት እንዳበሳጩ የደረሰን መረጃ አመልክቷል። በዚህም ምክንያት የቀረበው ሪፖርት "መጽደቅ የለበትም" በማለት ሰፊ ግፊት ማድረጋቸውንና ይህ አልሳካላቸው ሲል በምክር ቤቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በተቃውሞ እና በድምፀ ተዓቅቦ ቮት ማድረጋቸው ታውቋል።

በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዚህ አጀንዳ ላይ አስተያየት የሰጠው ፓርቲ ኢዴፓ ብቻ መሆኑም ታውቋል። በኢዴፓ በኩል "በአማራ ክልል የተከናወነው ቆጠራ Population census ሳይሆን Political census ነው" የሚል አስተያየት በማቅረብ ተቃውሞውን አስመዝግቧል። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኅብረት) ተወካይ አቶ ገብሩ ገ/ማሪያም በበኩላቸው የኦሮሞ ብሔርን የሚመለከት ጉዳይ በተነሳበት በሌላ ወቅት "ቆሜ እንድናገር ይፈቀድልኝ" ብለው ፓርላማውን እንዳላወኩ፣ በአማራ ክልል ጉዳይ ላይ የገኙው ፓርቲ አባላት ጫጫታ ሲያሰሙ አቶ ገብሩ "ስነ-ስርዓት" ብለው የመናር ዕድል ሲሰጣቸው "ምናለ ስብሰባውን ባትበጠብጡ" የሚል አስተያየት ማቅረባቸውን የደረሰን መረጃ ጠቅሶ፣ "ህብረቱ ለአንድ ክልል ብቻ መቆሙን አረጋግጧል" ሲል የዜና ምንጫችን አስተያየቱን አጠቃሏል።

የአማራ ህዝብ ቁጥር መቀነስ ከፌዴራል መንግስት ለክልሎች በሚመደብ በጀት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይታወቃል።